# የሜዲካል እንሹራንስዎን መረዳት

## የእንሹራንስ ሽፋንዎን ማራመድ



ልጅዎ የልዩ ጤና እንክብካቤ በሚያስፈልገው ጊዜ፣ የእድገት መዘግየት ወይም የአካል ጉዳት ላይ በሚሆንበት ጊዜ፣ የእንሹራንስ ሽፋንዎን መረዳት አስፈላጊ ነው። ስለ እርስዎ የጤና ኢንሹራንስ ጥቅማጥቅሞች እንዲሁም ኢንሹራንስ የልጅዎን የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም ለመደገፍ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል የበለጠ እንዲማሩ ይበረታታሉ። ከFamily Resources Coordinator (ከቤተሰብ ሃብት አስተባባሪዎ፣ FRC) እና የቅድመ ጣልቃ ገብነት ቡድን ጋር ለመጋራት ይህን መረጃ ለመሰብሰብ የተያያዘውን የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ደብተር ከተጨማሪ ዝርዝር ምክሮች ጋር መጠቀም ይችላሉ።

### ስለ እቅድዎ ይማሩ (ይወቁ)

የልጅዎን ፍላጎቶች ለማሟላት፣ ስለ ሽፋንዎ መማር በጣም ጥሩውን ውሳኔ ለማድረግ ይረዳዎታል። የእርስዎ የኢንሹራንስ ዕቅድ ሽፋንዎን የሚያጠቃልል እና የእርስዎን ኢንሹራንስ የሚቀበሉ እና/ወይም በአውታረ መረብዎ ውስጥ ያሉ አቅራቢዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ላይ አንዳንድ መመሪያ የሚሰጥ ሰነድ የማጠቃለያ ዕቅድ መግለጫ አለው። በቀጣሪዎ (አሰሪዎ) እና በኢንሹራንስ አቅራቢው ላይ በመመስረት ይህ የወረቀት ሰነድ ወይም በኦንላይን ላይ ገብተው ማንበብ የሚችሉት መረጃ ሊሆን ይችላል። ስለ እቅድዎ መረጃ ለማግኘት፣ የአሰሪዎን የሰው ግንኙነት ክፍል ወይም በኢንሹራንስ ካርድዎ ላይ ያለውን የአባል አገልግሎት መረጃ ያግኙ።

### ስለ እቅድዎ መጠየቅ የሚችሏቸው አጠቃላይ ጥያቄዎች

እቅድዎ ምን እንደሚሸፍን ከማወቅ መሰረታዊ ነገሮች በተጨማሪ ለሽፋን የሚያስፈልጉትን ህጎች መማር አስፈላጊ ነው፡-

- በልዩ ሙያተኛ ለመታየት እቅድዎ ከዶክተርዎ ወይም ከሌላ አገልግሎት አቅራቢዎ ሪፈራል ያስፈልገዋል?
- የቅድሚያ ጣልቃገብነት አገልግሎቶችን የሚሰጥ (ማለትም እንደ አካላዊ ቴራፒስት፣ የሙያ ቴራፒስት፣ የንግግር ቴራፒስት፣ የአመጋገብ ባለሙያ) የተለየ ቴራፒስት/ፕሮግራም ለማየት እቅድዎ ሪፈራል ያስፈልገዋል?
- ሪፈራልን እንዴት ነው የሚያገኙት? ቢሮ በመሄድ? በቅድመ ማሳወቅያ? ሌላ?
- እቅዱ በዓመት ውስጥ ምን ያህል የቴራፒ ጉብኝትን በውስጡ ይሸፍናል? ሪፈራሉ እድሳት ያስፈልገዋል? ለተጨማሪ ጉብኝቶች በስልክ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ? ወይስ ከዋናው ተንከባካቢ ሐኪም ጋር ሌላ ጉብኝት ቀጠሮ መያዝ ያስፈልግዎታል?
- ምን አይነት ቀጠሮዎች፣ ምርመራዎች እና ሂደቶች ናቸው የቅድመ-ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው? ዶክተሩ ቅድመ-ፈቃዱን ማግኘት ይችላል ወይንስ የጤና እቅድዎን በቀጥታ ማነጋገር አለብዎት?
- በእቅዱ (በአውታረ መረብ ውስጥ አቅራቢዎች) ለመሸፈን የተስማሙ አቅራቢዎችን ብቻ መጠቀም ይጠበቅብዎታል?
- እንዲሁም የእቅድዎ አካል ያልሆኑ ዶክተሮችን ወይም ሌሎች የህክምና ሰጪዎች አገልግሎት ማየት የሚችሉ ከሆነ (ከአውታረ መረብ ውጭ ሽፋን) እነዚህን ዶክተሮች ወይም በሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ለመታየት ዕቅዱ ምን ህጎች አሉት? ከአውታረ መረብ (ኔትዎርኩ) ውጪ ያለ አቅራቢን ለመጠቀም ምን ያስወጣዎታል?
- በድንገተኛ ጊዜ ወይም በሚጓዙበት ጊዜ በእቅድዎ አውታረ መረብ ወይም ኔትዎርክ የሚባለው ውስጥ ያልሆነ ዶክተር ወይም በሌላ አገልግሎት ሰጪ መታየት ይችላሉ? እንደዛ ከሆነ፣ ወጪው ለእርስዎ ምንድን ነው የሚሆንብዎ?


**መገናኛ:**

Department of Children, Youth & Families Early Support for Infants and Toddlers (የህፃናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ ለህፃናት እና ታዳጊዎች ፕሮግራም የቅድመ ድጋፍ) ፕሮግራም

PO Box 40970 Olympia, Washington 98504-0970 | **esit@dcyf.wa.gov**

**www.dcyf.wa.gov/services/child-development-supports/esit**



Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

## በሜዲካል አስፈላጊ ነው

የጤና እቅድዎ ምን አይነት ጥቅሞችን እንደሚሸፍን እና የሂሳብ አከፋፈል እንዴት እንደሚሰራ ቢያውቁም እንኳን የልጅዎን የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በማግኘት ላይ አሁንም ችግር ሊኖርብዎት ይችላል። "Medically Necessary (ለሕክምና አስፈላጊ)" የሚለው ቃል የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለአንድ የተወሰነ ሕክምና ወይም ሂደት የሕክምና ፍላጎት ለመወሰን የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ይህ ትርጓሜ ለልጅዎ ሊያስፈልገው ወይም ሊያስፈልጋት ለሚችሉ ህክምና እና ሂደቶች የክፍያ ሁኔታን ለመወሰን ያገለግላል።

ሁልጊዜውም ቢሆን የዕቅድዎን የሕክምና አስፈላጊነት ፍቺ መፈለግ አለብዎት፤ ማንኛውም የሕክምና አስፈላጊነት ትርጉም ለትርጉም በታ አለው። የሜዲካል ወይም ሕክምና አስፈላጊነትን ማረጋገጥ ካስፈለገዎት፣ በመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪዎ ወይም አገልግሎቱን በሚጠይቅ ሌላ የህክምና አገልግሎት ሰጪ ደብዳቤ ሊጻፍ ይችላል።

## እምቢታን መቃወም (ይግባኝ ማለት)

የጤና ፕላንዎ ለአንድ አገልግሎት ካልከፈለ ወይም አስቀድሞ በአገልግሎት ካልተስማማ፣ በጤና ዕቅዱ ውሳኔ ይግባኝ የማለት አማራጭ አለዎት። ኢንሹራንስ ለምን ለአገልግሎቱ እንደማይከፍል መረጃ ለማግኘት የእርስዎ FRC ወይም አገልግሎት አቅራቢ ከእርስዎ እና ከጤና እቅድዎ ጋር ሊሰሩ ቢችሉም፣ ይግባኝ የመጀመር ሃላፊነት አለብዎት። ለጤና እቅድዎ ይግባኝ ሂደት ላይ ያለው መረጃ በሽፋን ማስረጃ ውስጥ ነው። የጤና እቅድ ይግባኝ ሂደት ከጤና እቅድ ወደ ጤና እቅድ ይለያያል፣ ስለዚህ ሽፋንዎን በሚገመግሙበት ጊዜ እራስዎን ከሂደቱ ጋር በደንብ ማወቅ አለብዎት። የዕቅድዎ Explanation of Benefits (የጥቅማ ጥቅሞች ማብራሪያ፣ EOB) ፎርም አንድ አገልግሎት የተሸፈነ ወይም ያልተሸፈነ እንደሆነ ይነግርዎታል። እቅድዎ የተከለከለውን አገልግሎት የሚሸፍን መሆኑን ለማረጋገጥ የጤና እቅድዎ ለልጅዎ ሁሉንም አገልግሎቶች መሸፈን የለበትም እና በመጀመሪያ የሽፋን ማስረጃ ቡክሌትን ይመልከቱ። በአጠቃላይ፣ የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ:-

- አገልግሎቱ የተከለከለው በስህተት ነው ብለው ካመኑ፣ ስለ EOB ለመወያየት እቅድዎን በስልክ ማነጋገር ይችላሉ። ይህ መደበኛ ያልሆነ የግምገማ ሂደት ነው። በስልክ ጥሪ ይግባኝ ማለት ስለማይችሉ ከመደበኛ ግምገማ ማንኛውንም ውጤት በጽሁፍ ማግኘቱን ያረጋግጡ።
  - እያንዳንዱን የስልክ ጥሪ በእቅድዎ ላይ ያነጋገሩትን ሰው ስም እና የውይይቱን ማስታወሻ ይመዝግቡ። Health plan (የጤና እቅዱ) ተወካይ መረጃን ይዞ ወደ እርስዎ የሚመለስ ከሆነ፣ መቼ ምላሽ እንደሚጠብቁ ማወቅዎን ያረጋግጡ እና ተመልሰው ካልሰሙ የጤና እቅዱን ይከታተሉ።



- የደንበኛ አገልግሎት ተወካይዎ እቅድዎ አገልግሎትን እንደማይሸፍን ከተናገረ አሁንም ለሽፋን ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ወደ መደበኛ ይግባኝ ለመቀጠል ከፈለጉ፣ የጽሁፍ እምቢታ ያስፈልግዎታል።
  - መደበኛ ይግባኝ ለማቅረብ ከወሰኑ፣ ማመልከቻዎ በጽሁፍ መሆን አለበት።
    - የጤና እቅድዎ የይግባኝ ቅጽ ሊኖረው ይችላል።
    - እንደዛ ካልሆነ፣ የሽፋን ማስረጃው የይግባኝ ሂደቱን ይገልፃል።
    - ሁል ጊዜ የጽሁፍ አቤቱታታዎን ግልባጭ ያስቀምጡ።
- የሚከተሉትን መረጃ በይግባኝ ለማቅረብ ይጠብቁ
  - ስምዎን፣ አድራሻዎን፣ እና የስልክ ቁጥርዎን
  - የአባልነት መለያ ቁጥርዎ ወይም የ Social Security number (የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ)
  - Explanation of Benefits (የጥቅማ ጥቅሞች ማብራሪያ፣ EOB) ቅጾች ቅጂዎች እና የአቅራቢዎ ስም እና የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ
  - መሸፈን የሚፈልጉትን የአገልግሎት ወይም የአሰራር መግለጫ
  - አገልግሎቱ ለምን ሽፋን ማግኘት እንዳለበት የሚደግፍ መረጃ

ይግባኝዎን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ማስገባት ሊጠበቅብዎ ይችላል። ከተፈቀደው ጊዜ ውጭ የሚቀርቡ ይግባኞች በጤና አቅዱ (ፕላኑ) ውስጥ ከግምት አይገቡም። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ እቅዱ ለአስቸኳይ ጉዳዮች ልዩ አሰራር ሊኖረው ይችላል።

በWashington ግዛት ውስጥ ስላሉት የኢንሹራንስ ደንቦች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ወደ ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎች የስልክ መስመር በ 1-800-562-6900 ላይ በመደወል ያግኙ።

በልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎት፣ የእድገት መዘግየት ወይም አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ህጻናት ስለ ጤና እንክብካቤ ፋይናንስ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ወደ Washington ግዛት የቤተሰብ ድምጽ በ 1-800-5-PARENT ይደውሉ።

# የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ዎርክሺት

የልጁ ስም፦ ________________ የወላጅ ስም፦ ________________

የልጁ DOB፦ ________________ የልጁ ምርመራ ዉጤት፦ ________________

ባለሞያን መጠቆም፦ ________________

*የእንሹራንስ መረጃ፦ እባክዎን ወደ ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ይደውሉ እና ይህንን ቅጽ በተቻለዎት መጠን ይሙሉ። ስለ ሽፋንዎ የማያውቁት ከሆነ ይህ በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ ነው።*

የእንሹራንሱ ስም፦ ________________ ስልክ፦ ________________

የይገባኛል ጥያቄ አድራሻዎች፦ ________________

እንሹራንስ የተሰጠው ሰው ስም፦ ________________ ID #፦ ________________

እቅድ/ቡድን #፦ ________________ ደምቡ ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፦ ________________

ሲደውሉላቸው፣ ለቀጣይ ማጣቀሻ የሚያናግሩትን ሰው ስም መጻፍዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

ተጠሪ ሰው፦ ________________ ቀን፣ የመደወያ ጊዜ፦ ________________

"ለነርቭ ልማት ጥቅሞቼን እና ሽፋኑን ለማብራራት እየደወልኩ ነው" ይበሉ። (የአባልነት ID # ቁጥርዎን ይጠይቅዎታል #) ሁሉንም መረጃ ለማሙላት በቂ የሆነ ጥያቄ ይጠይቁ። ሙሉ ያልሆነ መረጃ ሌላ የስልክ ጥሪ ይፈልጋል።

የእኔ ቴራፒስት/የEI ፕሮግራም፣ ________________ ፣ በተሳታፊ አገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር ውስጥ ነው?

የእርስዎ ቴራፒስት/የEI ምርጫ በአውታረ መረቡ (በኔትዎርኩ) ውስጥ ከሌለ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቁ፦

"የእኔ ደምብ (ፖሊሲ) የራሴን ቴራፒስት እንድመርጥ ይፈቅድልኛል?" ________________

________________

________________

"ከኔትወርኬ ወይም ከአቅራቢው ዝርዝር ውጭ መሄድ እችላለሁ?" (እንደዛ ከሆነ፣ "የእኔ ሽፋን የተለየ ነው? እናም ምንድን ነው ልዩነቱ? ለልዩነቱ ክፍያ ልጠየቅ እችላለው?") ________________

________________

ከዛን በኋላ ይህን ይጠይቁ፦ "የእኔ"፦

Co-pay (የጋራ ክፍያ)፦________ % ወይም $ ________ /ክፍለጊዜ ምንድን ነው። የጋራክፍያዬ or የጋራ እንሹራንሴ የሚታሰበው በቀን ነው ☐ ወይስ በቴራፒ ነው? ☐

ለምሳሌ፣ ልጅዎ OT እና የንግግር ቴራፒ ከታየ እና $15 የጋራ ክፍያ ካለዎት፣ ምን ያህል የሕክምና ዘዴዎች ቢያዩም በአንድ ሕክምና $15 ዶላር በድምሩ $30 ዶላር ወይም በቀን $15 ዶላር ብቻ ዕዳ አለብህ?

ተቀናሽ ነው? ☐ አይ ☐ አዎ የሚቀነሰው መጠን $ ________ / የቤተሰብ ወይስ የግል?

በካላንደር ዓመቱ የሚቀነስ ነው? ☐ አዎ ☐ አይ የወራዊ ተቀነሽ የሚጀምረው፦ ________

ለዚህ ዓመት ምንም አይነት ተቀናሽ ተደርጎ ያውቃል? ☐ አዎ ☐ አይ አዎ ከሆነ፣ ምን ያህል? ________

በጥቅማጥቅም ዓመቴ ያሉ ቀንዎች ምንድን ናቸው፦________ ለ ________

ከኪሴ የማወጣው ከፍተኛ ወጪ ምንድን ነው? ________

ከፍተኛው ላይፍታይሜ ስንት ነው? $ ________ እስከ ዛሬ ድረስ ምን ያህል ተሟልቷል? $ ________

ከፍተኛው የህይወት ዘመን በቤተሰብ ነው ወይስ በአንድ ሰው ነው የሚለካው? ________

በዓመት ምን ያህል ጉብኝቶች፣ ________

በአንድ የሕክምና ጉብኝት ለOT፣________ ለPT ________ እና ለንግግር ይፈቀዳሉ? (ስለ ሁሉም ሕክምናዎች ይጠይቁ -የ Occupational Therapy (የሙያ ቴራፒ፣ OT)፣ Phsical Theraphy (አካላዊ ቴራፒ፣ PT) እና Speech Theraphy (የንግግር ሕክምና፣ ST) - ምንም እንኳን ልጅዎ አንድ ብቻ ቢፈልግ, ስለዚህ ለወደፊቱ እንደገና መደወል የለብዎትም)

እስከዛሬ ድረስ የተጠቀሙባቸው ጥቅማጥቅሞች አሉ? ☐ አዎ ☐ አይ አዎ ከሆነ፣ ያብራሩ፡-_____________

ከመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢዬ ቅድመ ፍቃድ ያስፈልጋል? ☐ አዎ ☐ አይ

እንደ OT፣ PT፣ እና ንግግር ላሉት ልዩ አገልግሎቶች ከየመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪዬ ቅድመ-ፍቃድ ያስፈልጋል? ☐ አዎ ☐ አይ

የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢ ማዘዣዬ ያስፈልጋል? ☐ አዎ ☐ አይ

እንደ OT፣ PT፣ እና ንግግር ላሉት ልዩ አገልግሎቶች የእኔ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢ ማዘዣ ያስፈልጋል? ☐ አዎ ☐ አይ

አዎ ከሆነ፣ ጉብኝቶችን አስቀድሞ ለመፍቀድ ወይም የሐኪም ማዘዣ ለመስጠት (ማለትም፣ የሕክምና መዝገቦች፣ የሐኪም ማዘዣ፣ ግምገማ፣ የሕክምና አስፈላጊነት ደብዳቤ፣ ወዘተ) የሚፈልጉትን ይጠይቁ፡- ____________________

____________________

____________________

ፈቃዱ/የመድሀኒት ማዘዣው ስንት ክፍለ ጊዜዎችን ይሸፍናል፡- ____________________

የፈቃድ/የመድሀኒት ማዘዣው በየትኞቹ ጊዜያት ነው የሚሸፍነው ፡- ____________________ ለ ____________________

ሄደን ታይተን ከጨረስን በኋላ ተጨማሪ ለመታየት ማጸደቅ እንችላለን? ☐ አዎ ☐ አይ

የሚከተሉት ኮዶች ሽፋን አግኝተዋል?

| ቴራፒ (ሕክምና) | ኮድ | አዎ | አይ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

የእኔ ደምብ እንደ "ህክምና የሚሸፈነው ጉድለቱ በአደጋ፣
በህመም ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ከሆነ ብቻ ነው" የሚሉ የማግለል አንቀጾች አሉት? ☐ አዎ ☐ አይ

አዎ ከሆነ፣ የትኛው አንቀጽ ላይ ነው፡-____________________

የይገባኛል ጥያቄዎን ወደ የትኛው አድራሻ ነው የሚልኩት? ____________________

____________________

***ሁለተኛ ደረጃ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ካለዎት፣ ለዚያ ኢንሹራንስ ከነዚህ ቅጾች ውስጥ ሌላ አንዱን ይሙሉ።

ለህክምና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚከፍል የጤና ቁጠባ ሂሳብ ወይም ሌላ አይነት ሂሳብ ካለዎት፣ እነዚህ ጥቅማጥቅሞች ለቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ከአገልግሎት አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።



*DCYF አድሎ አይፈጽምም እንዲሁም ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣
የጋብቻ ሁኔታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ዕድሜ፣ የአርበኛነት ሁኔታ ወይም ማንኛውም የአካል፣ የስሜት ህዋሳት ወይም የአዕምሮ እክል ሳይኖር ለሁሉም ሰው ፕሮግራሞቹን እና አገልግሎቶቹን በእኩልነት ያቀርባል።*

*የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎን የDCYF Constituent Relations(የ DCYF የመሰብሰቢያ ግንኙነቶችን) በ 1-800-723-4831 ወይም በኢሜል* ***communications@dcyf.wa.gov****.*

DCYF PUBLICATION FS_0034 AM (07-2023) Ahmaric